'ሰውዬው በህብረት የሚሰግደው ሶላት በቤቱ ወይም በሱቁ ከሚሰግደው ሶላት ሀያ ምናምን ደረጃ ትበልጣለች።

ከአቡ ሁረይራ (ረዲየሏሁ ዐንሁ) - አላህ መልካም ሥራቸውን ይውደድላቸውና - እንደተላለፈው እንዲህ አሉ፦ "የአላህ መልክተኛ (የአላህ ሶላትና ሰላም በእርሳቸው ላይ ይስፈንና) እንዲህ ብለዋል፦ 'ሰውዬው በህብረት የሚሰግደው ሶላት በቤቱ ወይም በሱቁ ከሚሰግደው ሶላት ሀያ ምናምን ደረጃ ትበልጣለች። ይህም አንዳቸው ዉዱእ ሲያደርግ ዉዱእን አሳምሮ ከዚያም ከሶላት በስተቀር ሳያንቀሳቅሰው ከሶላትም በስተቀር ሌላን ሳይፈልግ ወደ መስጅድ ከመጣ መስጂድ እስኪገባ ድረስ በሚራመደው እያንዳንዱ እርምጃ ልክ
ለርሱ ደረጃው ከፍ ይደረግለታል፤ ወንጀሉም ከርሱ ላይ በሷው ይራገፍለታል። መስጂድ የገባ ገዜም በሶላቷ ምክንያት እስከተጠመደ
ድረስ ሶላት ውስጥ ነው። አንዳችሁ በሰገደበት ስፍራ ላይ እስከዘወተረ ድረስም ሰዎችን እስካላወከና ዉዱእ እስካላጠፋ ድረስ
መላእክቶች በርሱ ላይ ሶለዋት ያወርዳሉ። 'አላህ ሆይ እዘንለት፣ አላህ ሆይ ማረው፣ አላህ ሆይ ፀፀቱን ተቀበለው' ይላሉም።'"
[ሶሒሕ ነው።] [ቡኻሪና ሙስሊም ዘግበውታል።]

ነቢዩ (የአላህ ሶላትና ሰላም በእርሳቸው ላይ ይስፈንና) አንድ ሙስሊም በህብረት የሰገደ ጊዜ ይህቺ ሶላቱ ቤቱ ውስጥ ወይም ሱቁ ውስጥ ከሚሰግደው ሰላት ሀያ ምናምን እጥፍ የምትበልጥ መሆኗን ተናገሩ። ቀጥለውም የዚህን ምክንያት ተናገሩ። እርሱም ሰዉዬው ዉዱእን አሟልቶና አሳምሮ አድርጎ ከዚያም ሶላትን ብቻ ፈልጎ ወደ መስጊድ እስከወጣ ድረስ በእያንዳንዷ እርምጃው ምክንያት ደረጃው ከፍ ይላል፤ ወንጀሉም ይታበስለታል። መስጂድ ገብቶም ሶላትን እየጠበቀ ከተቀመጠ ሶላትን እስከተጠባበቀበት ጊዜ ድረስ የሶላትን ምንዳና አጅር ያገኛል። መላእክቶችም የሰገደበት ስፍራ ላይ እስከተቀመጠ ድረስ ለርሱ እንዲህ እያሉ ዱዓ ያደርጉለታል፦ "አላህ ሆይ ማረው፣ አላህ ሆይ እዘንለት፣ አላህ ሆይ ፀፀቱን ተቀበለው" ይህ ግን ዉዱኡን እስካላበላሸ ወይም ሰዎችን ወይም መላእክትን የሚያውክ ነገር እስካልፈፀመ ድረስ ነው።

http://sunnah.global/hadeeth/am/show/4566